# ምዕራፍ ሁለት

## ቅዱሳን መላእክት

ቅዱስ ማለት በቁሙ የተቀደሰ ክቡር ምስጉን ልዩ ምርጥ ንጹህ ጽሩይ ማለት ነው (36) ቅዱሳን የሚለው ቃል ደግሞ የቅዱስ ዘር ሲሆን የእግዚአብሔር ገንዘብ የሆኑ ሁሉ የሚጠሩበት ስም ነው ።

መላእክት ስንል ደግሞ መልእክተኛ አገልጋይ ማለት ነው (37)

ከላይ ትርጉማቸውን የሰጠነውን ሁለቱን ቃላት ስናገጣጥም ቅዱሳን መላእክት የሚል ዓረፍተ ነገር እናገኛለን ። የተቀደሱ መልእክተኞች የተመሰገኑ መልእክተኞች ንጹህ ምርጥ መልእክተኞች ማለት ነው ። እንግዲህ ቅዱሳን መላእክት እንዳሉ ሁሉ እርኩሳን መላእክትም አሉ ። እነርሱም ቀድሞ ቅዱሳን ሆነው የተፈጠሩ ኋላ ግን በሥራቸው ውዱቃን የሆኑ ሠራዊት አጋንንት ናቸው ።

የቅዱሳን መላእክት ከተማቸው ኢዮር ፡ ራማ ፡ ኤረር ፡ ተብሎ ይጠራል ። ከሰባቱ ሰማያት ውስጥ ናቸው ። ዲያብሎስና ሠራዊቱ ግን በእንጦርጦስ ገደል በባርባሮስ ጽልመት ተወርውረዋል ። ራዕይ ፲፪ ፡ ፱ ።

## የመላእክት ተፈጥሮ

በመላእክት ተፈጥሮ ላይ የተለያዩ ሐሳቦች በሊቃውንቱ ዘንድ ይሰነዘራሉ አንዳንዶቹ የመላእክት ተፈጥሮ ከእሳትና ከነፋስ ነው ። ለዚሁም ማስረጃ የብርሃነ ዓለም ጳውሎስ የዕብራውያን መልእክት ፩ ፡ ፯ ነው ብለው ያቀርባሉ በዚህ መልእክት ላይ «መላእክቱን ነፋሳት የሚላኩትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው» የሚለውን ዓረፍተ ነገር በ[illegible]ሲድ ነው ። ሌሎቹ ሊቃውንት ደግሞ ሲተረጉሙ ይኸ

(36) ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት
(37) የመ. ቅ መዝገበ ቃላት ገጽ 16



www.ethiopianorthodox.org

የሚያመለክተው መላእክት በእሳት በነፋስ መመሰላቸውን እንጂ ተፈጥሮአቸው ከእሳት ከነፋስ መሆኑን አይደለም ይሉና በእሳት በነፋስ የተመሰሉበትን ሲተነትኑ ነፋስ ፈጣን ነው መላእክትም ፈጣኖች ናቸው ። ነፋስ ረቂቅ ነው መላእክትም ረቂቃን ናቸው ። እሳት ብሩህ ነው መላእክትም ብሩሃን አእምሮ ናቸው ። እሳት ነፋስ ፈጻምያን ፈቃድ ናቸው መላእክትም ፈጻምያን ፈቃድ ናቸውና ። ስለዚህ ነው በእሳት በነፋስ የመሰላቸው ይላሉ ። ታዲያ ከምን ተፈጠሩ ሲባሉ አክሲማሮስ የተባለ ሊቅ እንዳስረዳው የመላእክት ተፈጥሮ «እምኀበ አልቦ» ወይም ከአምላካዊ ብርሃን ነው ። «የመላእክት ተፈጥሮ ከአምላካዊ ብርሃን ነው ከነፋስ ከእሳትስ ተፈጥረው ቢሆኑ አንደኛ ሙተው በፈርሱ በበሰበሱ ነበር ።» በኋል ብለው ይናገራሉ ። (38)

## መላእክት ምን ቀን ተፈጠሩ

መላእክት በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ እንደተፈጠሩ ይነገራል ። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በጉልህ በዚህ ቀን ተፈጠሩ ብሎ ባይናገርም ዳሩ ግን በዕለተ እሑድ መፈጠራቸውን በአንዳንድ ቦታ ሳይጠቁም አላለፈም ።

ሳዊሮስ ዘእስሙናይን የተባለ የቤተክርስቲያን ሊቅ መላእክት የተፈጠሩ ለይኩን ብርሃን (ብርሃን ይሁን) ባለ ጊዜ ሥጋ የሌላቸው ረቂቃን አድርጎ እሑድ በመጀመሪያው ሰዓት ከብርሃን ነው የፈጠራቸው ብሏል ።

ቅዱስ ዳዊትም «መላእክት ሁሉ አመስግኑት ጸሐይና ጨረቃ ከዋክብት ብርሃን ሁሉ አመስግኑት እርሱ ብሎአልና ሁኑም እርሱም አዝዞአልና ተፈጠሩም » መዝ ፻፵፰ ፣ ፪—፭ ብሎ መላእክት በመጀመሪያው ቀን በዕለተ እሑድ መፈጠራቸውን ገልጿአል ። ቀሌምንጦስም «በመጀመሪያው ቀን እሑድ ሰማይንና መላእክትን ሁሉ ፈጠርኩዋቸው ይህንም ለሙሴ አልነገርኩም» ይላል (39)

---

(38) የቅዱስ ጳውሎስ መጽ ንባቡ ከነትርጓሜው ገጽ 612, መርሐጽ ድቅ ባህለ ሐይማኖት ገጽ 35

(37) መርሐ ጽድቅ ባሕለ ሃይማኖት ገጽ 34



## የመላእክት ባህርይ

መላእክት በፍጥረታቸው ረቂቃን መናፍስት ስለሆኑ ሥጋና አጥንት የላቸውም አያገቡም አይጋቡም ፣ አይበሉም አይጠጡም ። ይህንንም መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስረዳው እውነት ነው ማቴ ፳፪ ፣ ፴። ሊቃ ፳፬ ፣ ፴፱ ።

መጽሐፍ ቅዱስን እንዳሻቸው የሚተረጉሙ አንዳንዶች ግን ዘፍ ፮ ፣ ፪ ያለውን በመጥቀስ መላእክት ያገባሉ ይጋባሉ እያሉ ያስተምራሉ ። በዚህ ቦታ «የእግዚአብሔር ልጆች የሰውን ሴቶች ልጆች አገቡ» ማለቱ መላእክት የሰውን ሴት ልጆች አገቡ በፍትወት ረከሱ ማለት አይደለም ።

በእርግጥም መላእክት በመጽ ኢዮብ ፩ ፣ ፮ ላይ እንደተጠቀሰው «የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉ ። ግን የእግዚአብሔር ልጆች የሚለው አነጋገር ሁል ጊዜ ለረቂቃን መላእክት ብቻ የሚነገር አይደለም ። በዘፍ ፮ ፣ ፪ መላእክት (የእግዚአብሔር ልጆች) የተባሉት ረቂቃን መላእክት ሳይሆኑ ሰዎች ናቸው ። ሥጋና አጥንት ያላቸው ሰዎች እንጂ በቁሙ መላእክት አይደሉም ። በደብር ቅዱስ ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው ይኖሩ የነበሩ ደቂቃ ሴት ናቸው ። ስለምን (የእግዚአብሔር ልጆች) አላቸው ቢባል ስለ ሁለት ነገር ነው ።

፩ኛ/ ስለአለቅነታቸው

፪ኛ/ ስለንጽሕናቸውና ስለቅድስናቸው ነው ።

፩ኛ/ <u>ስለአለቅነታቸው</u> ፡— ለተባለው መልአክ የግእዝ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አለቃ ማለት ነው መላእክት አለቆች ይሆናል ። መጽሐፍ ቅዱስም በዚህ መንፈስ ቃሉን ተጠቅሞበት እናገኛለን ።

ዮሐንስ ራዕይ ፪ ፣ ፩,፰,፲፪ ። ፫ ፣ ፩, ፯,፲፬ በእነዚህ ቦታዎች «ወደ ቤተክርስቲያን መልአክ እንዲህ ብለህ ጻፍ » ማለቱ ለነሚካኤል ፣ ለነገብርኤል ማለቱ ሳይሆን ለቤተክርስቲያናቱ አለቆች ማለቱ ነው ። የዚህ ደብር አለቃ እንደሚባለው ማለት



www.ethiopianorthodox.org

ነው ። ደቂቃ ሴትም መላእክት መባላቸው አለቆች ስለሆኑ ነው ።

፱ኛ/ ምክንያት ስለንጽሕናቸውና ስለ ቅድስናቸው ፤

ሰዎች ሰብአዊ ባህርይ ብቻ አይደለም ያላቸው ማንኛውም ሰው የእንስሳት ባህርይ፣ የመላእክት ባህርይ፡እንዲሁም ሰዋዊ ባህርይ ይታይበታል ። ግዜ ሳይወስን የሚበላ የሚጠጣ ። እንዲሁም ከሥርዓት ውጥቶ ሥርዓት እንደሌላቸው እንደ እንስሳት የሚኖር ከሆነ እንስሳዊ ጸባይ አይሎበታል ይባላል ። ከእህል ከውሃ ርቆ ንጽህ ጠብቆ በጾም በትኅርምት እግዚአብሔርን እያመሰገነ ሲኖር መልአካዊ ጸባይ ተላብሷል ይባላል ። ጾም በመልአካዊ ሥርዓት ውስጥ መግባት ነው ። ግዜ ወስኖ መብላት መጠጣት በሕጉ በትእዛዙ መኖር ሰብአዊ ጸባይ ነው ። እንግዲህ በደብረ ቅዱስ ይኖሩ የነበሩ ደቂቀ ሴት ከሴት ርቀው ንጽሕ ጠብቀው በጾም በጸሎት ገዳም ገድመው ከቃየል ልጆች ተለይተው ይኖሩ ስለነበር የእግዚአብሔር ልጆች (መላእክት) ተብለው ይጠሩ ነበር ። በአንጻሩ ደግሞ የቃየል ልጆች የራሳቸውን ስም ለማስጠራት ብቻ የሚጥሩ ሥጋዊ ጸባይ ያየለባቸው ስለነበር የሰው ልጆች ተባሉ ። እነዚህ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉ ደቂቀ ሴት አንድ ቀን የቃየልን ልጆች አይተው በመልካቸው ማማር ተማርከው በፍትወት መነደፋቸውን በዝሙት መውደቃቸውን ሙሴ ሲጽፍ የእግዚአብሔር ልጆች ከሰው ልጆች ጋር በፍትወት ረከሱ ብሎ ጻፈ ። ሄኖክ የእግዚአብሔር ልጆች የተባሉት ደቂቀ ሴት መሆናቸውን ገልጾ ጽፏል መጽ. ሄኖክ ፪ ፡ ፩—፫ (40)

ደግሞም ዛሬም ንጽሕናቸውን ቅዱስናቸውን የጠበቁ ካሉ እንደ ደቂቀ ሴት የእግዚአብሔር ልጆች ተብለው እንደሚጠሩ መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስገነዝበን ነው ። «የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ» ፩ኛ የዮሐንስ መልእክት ፫ ፡ ፩ ።

(40) ኲኲሐ ሃይማኖት ገጽ 76-79



ከእግዚአብሔር በጥምቀት የተወለደ ሁሉ የእግዚአብሔር ልጅ ይባላል ። ነገር ግን መላእክት ነን ማለት አይደለም ። ስለዚህ ሙሴ ጌታ ያለውን «መላእክት አያገቡም አይጋቡም» ብሎ የተናገረውን አስተባብሎ አገቡ ማለቱ አይደለም ። ፍትወት ሥጋ በለበሰው ላይ እንጂ በረቂቃን መላእክት ባህርይ የለም ።

# የመላእክት አገልግሎት

መላእክት እግዚአብሔርና ሰውን ያገለግላሉ ። እግዚአብሔርን ያለ እረፍት ያመሰግኑታል በመንበሩ ዙሪያ ሆነው ያለማቋረጥ ቅዱስ ፣ ቅዱስ ፣ ቅዱስ የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ምድር ሁሉ በክብሩ ተሞልታለች እያሉ ያመሰግናሉ ። ኢሳ ፮ ፡ ፪—፫ ራዕይ ፬ ፡ ፬—፲፩ የመላእክት ምግባቸው መጠጣቸው ስብሐተ እግዚአብሔር ነው ። እግዚአብሔርን ከማመስገናቸውም በተጨማሪ ወደ ላካቸው ሥፍራ በፍጥነት ይሔዳሉ ።

መላእክት ሰውን የሚያገለግሉት በተራዳኢነታቸው በአማላጅነታቸው ነው ። ከፈጣሪ አማልደው ምህረትን ያሳጣሉ ። ይኸም የመላእክት አገልግሎት በአንድ መንገድ ብቻ ሳይሆን በሁለት መንገድ ነው ከእግዚአብሔር ዘንድ ምህረትን ይዘው እንደሚመጡ ሁሉ የሰዎችን ልጆች ልመናም ወደ እግዚአብሔር ይዘው ይወጣሉ ።

## ስለ ተራዳኢነታቸው

መዝ ፺/፺፩ ፡ ፲፩ «በመንገድህ ሁሉ ይጠብቅህ ዘንድ መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል በእጆቻቸው ያነሡሃል ።

ከእዚህ አባባል እንደምንረዳው መላእክት በእግዚአብሔር የታመነን ሰው ሁሉ በሚሄድበት መንገድ ሁሉ አብረው በመሄድ ችግር እንዳይገጥመው በስውር እንደሚጠብቁት ነው ።

ኦሪት ዘፍጥ ፵፰ ፡ ፲፮ «አባቶቼ አብርሃምና ይስሐቅ በፊቱ የሄዱለት እርሱ እግዚአብሔር ከታናሽነቴ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ እኔን



www.ethiopianorthodox.org

የመገበኝ እግዚአብሔር ከክፉ ነገር ሁሉ ያዳነኝ መልአክ እርሱ እነ ዚህን ብላቴኖች ይባርክ»

ያዕቆብ የተራዳውን መልአክ ስም ጠርቶ ምናሴንና ኤፍሬምን እንዲባርክ ጠይቋል ። ስለዚህ ዛሬ እኛስ ያዕቆብን አብነት አድር ገን ሊቀመልአክት ቅዱስ ሚካኤል እንዲሁም ቅዱስ ገብርኤልንና ሌሎችን መላእክት በወርቅ መስቀላችሁ ባርኩን እርዱን ብንል ከመ ጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሚያሰኝ ምኑ ነው?

— ትንቢተ ዳንኤል ፫ ፡ ፳፬—፳፰ ሦስቱን ሕጻናት መልአኩ ቅዱስ ገብርኤል ተራድቷአቸዋል ።

— ዳንኤል ፮ ፡ ፳፪ «አምላኬ መልአኩን ልኮ የአንበሶችን አፍ ዘጋ» ዛሬም መላእክት እንደተራበ አንበሳ አፉን ከፍቶ ሊውጠን የሚያጋሣውን ሰይጣንን ቅዱሣን መላእክት አፉን እንዲዘጉልን ብንጠራቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ ያሰኛል ?

— መዝሙር ፴፫(፴፬) ፡ ፩ «የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል ፡ ያድናቸውማል»

ከዚህ እንደምንረዳው መላእክት በሚያከብራቸው በሚወዳቸው በአማላጅነታቸው በሚተማመን ሰው (ጉባኤ) መካከል በመገኘት ከማ ንኛቸውም መጥፎ ነገር ያድኑ አቸውማል ። ክብርን ለሚገባው ክብርን መስጠት እንዳለብን መጽሐፍ ቅዱስ ያስተምረናል ። ስለሆነም የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ብቻ ሲሰፍርና ሲያድናቸው በማይፈሩት (በማያከብሩት ሰዎች ዘንድ ግን እንደ ማይገኝ ዳዊት ያስገነዝባል ።

— ኦሪት ዘጸ ፳፫ ፡ ፳ «በመንገድህ ይጠብቅህ ዘንድ ወዳዘጋጀሁትም ስፍራ ያገባህ ዘንድ እነሆ እኔ መልአክን በፊትህ እሰድዳለሁ ። በፊቱ ተጠንቀቁ ቃሉንም አድምጡ ስሜም በእርሱ ስለሆነ ኃጢ አት ብትሠሩ ይቅር አይልምና አታስመርሩት»

ይቅር አይልምና አታስመርሩት ማለቱ መላእክት ከእግዚአብሔር የተሰጣቸው ሥልጣን እንዳላቸው ማመልከቱ እንደሆነ ግልጽ ነው ።



ልናስመርራቸው አይገባም ። ብናሳዝናቸው ግን ይቅር አይሉንም ለዚ ህም አብነት የሚሆነን የካዘርያስ ታሪክ ነው

ዘካርያስ የመልአኩ የቅዱስ ገብርኤልን ቃል ባለመስማቱ በመ ጠራጠሩ ቅዱስ ገብርኤል ዲዳ እንዳደረገው በሉቃ ፩ ፡ ፳ ላይ የሰፈረ ነው ። አመጣጡ ለብስራት ነበር ዳሩ ግን ዘካርያስ ስላስቆጣው ነበር ያልመጣበትን ፍርድ የፈረደበት እንግዲህ መላእክት ከእግዚአብሔር መላክ ብቻ እንጂ ሌላ ማድረግ አይችሉም ከተባለ ቅዱስ ገብርኤል የተላከው ለብሥራት ነበር ታዲያ ያልተላከበትን ዲዳ ማድረግ ለምን ሲፈጽም እግዚአብሔር አልተቆጣውም?

ትንቢተ ዳንኤል ፲ ፡ ፲፫ «የፋርስ መንግሥት አለቃ ግን ሃያ አንድ ቀን ተቋቋመኝ እነሆም ከዋነኞቹ አለቆች አንዱ ሚካኤል ሊረዳኝ መጣ እኔም ከፋርስ ነገሥታት ጋር በዚያ ተውሁት»

በመላእክት ተራዳኢነት ማመን በሌላ አምላክ ማመን ማለት አይደለም ። ለዚህም ዳንኤል ራሱ ምሥክር ይሆናል የፋርስ መን ግሥት አለቃ (ሰይጣን) በተቋቋመው ጊዜ የታላቁን መልአክት የቅ ዱስ ሚካኤልን ረዳትነት ሽቷል ። ቅዱስ ሚካኤል ሊረዳው መመ ጣቱን ጠቅሷል እንግዲህ ዳንኤልን የመሰለ የእግዚአብሔር ሰው የመ ልአኩን እርዳታ ሲሻ እኛ ግን በራሳችን ጸሎት ብቻ ተጠብቀን እን ኖራለን ብንልና የመላእክትን ተራዳኢነት ብንንቅ ከእግዚአብሔር ጸጋ በአፉ (ውጭ) እንደሆንን ልንረዳው ይገባናል ። የትዕቢት መን ፈስ ያደረብን መሆኑንም መግለጻችን ነው ።

መላእክት ከጥንቱ የተፈጠሩት ሰውን ሊረዱ ሊራዱም ጭምር ነው ። ስለዚህ በመላእክት አማላጅነት መታመኑ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው ። ዳንኤል በም ፲፪ ፡ ፩ «ስለ ሕዝብህ ልጆች የሚቆመው ታላቁ አለቃ ሚካኤል ይነሣል» በማለት መላእክት በአማላጅነታቸው ለሚ ተማመኑ ለእግዚአብሔር ልጆች በተራዳኢነት እንደሚቆሙላቸው ገልጹአል ።

መላእክት ስለ ሰው ልጆች መጸለይ (ማማለድ) እንደሚችሉ ነብየ እግዚአብሔር ዘካርያስ ገልጾአል «......የእግዚአብሔር መልአክ መልሶ አቤቱ የሠራዊቱ ጌታ ሆይ እነዚህን ሰባ ዓመት የተቆጣ ሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከመቼ



www.ethiopianorthodox.org

ነው? አለ... እግዚአብሔርም መልሶ ከእኔ ጋር ይነጋገር ለነበረው መልአክ በመልካምና በሚያጽናና ቃል ተናገረው ። ስለዚህም ከእኔ ጋር ይነጋገር የነበረው መልአክ እንዲህ አለኝ ስበክ እንዲህም በል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሐር እንዲህ ይላል ።... ወደ ኢየሩሳሌም በምሀረት ተመልሻለሁ» ትን ዛካ ፩ ፣ ፲፪—፲፯ ።

እንግዲህ መልአኩ «ሰባ ዓመት ሙሉ የተቆጣሃቸውን ኢየሩሳሌምንና የይሁዳን ከተሞች የማትምራቸው እስከ መቼ ነው?» የሚለው ጥያቄ የአማላጅነት ጥያቄ ነው ። ማራቸው እንጂ ግለት ነው ይህም ጥያቄ የልመና ዓይነት መሆኑን ለማረጋገጥ ብንሻ የእግዚአብሔርን መልስ ማስተዋል ነው ። እግዚአብሔር የመልአኩን አማላጅነት ስለተቀበለ ወደ እስራኤል በምሀረት መመለሱን ለመልአኩ ነገረው ። መልአኩም አማላጅነቱ ተቀባይነት ስላገኘ ወደ ዘካርያስ አስተላለፈ ። እንግዲህ እግዚአብሔር መልአኩ ፩ኛ/ ስለ እስራኤል ሕዝብ ሊያማልድ ወደ ፈጣሪው በቀረበ ጊዜ «ምን አገባህ አንተን በሥራዬ ምን ጥልቅ አደረገህ» ብሎ የቁጣ መልስ አልሰጠውም ። ይልቁንስ የመልአኩን ባለሟልነት ይገልጽ ዘንድ በመልካምና በሚያቆላምጥ ቃል ተናገረው እንጂ ። ትሁቱ ጌታ ከኃጢአት በስተቀር የሚያስቆጣው ነገር ስለሌለ የመልአኩን ርህራሄና አማላጅነት እንደ ወደደለትና አስደሳች የሆነ መልስ እንደሰጠው ጤናማ አእምሮ ያለው ሁሉ የሚያስተውለው ነው ።

— ሉቃ ወን. ፲፫ ፣ ፲—፱ «እንዲህ ብሎ መሰሰላቸው አንድ ሰው በታወቀች በወይኑ ቦታ ውስጥ በለስ ነበረችው ፍሬ ሊለቅም ወደ እስዋ ሔደ አላገኘም የወይኑን ጠባቂም የዛችን በለስ ፍሬ ሊለቅም ሲመላለስ እነሆ ሦስት ዓመት ነው አላገኘሁም እንግዲህስ ምድራችንን እንዳታቦዝን ቁረጣት አለው እሱም መልሶ እንዲህ አለው ። አቤቱ የዘንድሮን እንኳ ተዋት ዙሪያዋን ቆፍሬ አፈር እስከአስታቅፋት ፍግ እስከ አፈስባት ድረስ ። ምናልባት ለከርሞ ታፈራ እንደሆነ ያለዚያ ግን እንቆርጣታለን»

የምሳሌው ትርጉም ፦ እንደሚከተለው ነው ፤

— አንድ ሰው የተባለው እግዚአብሔር (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ) ነው



— በበለስ የተመሰለችው አንድም ቤተ እስራኤል ነች እንዲሁም በምድር ላይ ያሉ ሰዎች ናቸው ።

— የወይን ቦታ ሰራተኛ (ጠባቂ) መላእክት ናቸው ።

ት ን ታ ኔ ፤

፩ኛ/ እግዚአብሔር የሰውን ሥጋ ተዋሕዶ (ሰው ሆኖ) ሕግ በሚጠብቁባት በኢየሩሳሌም ያሉትን አይሁድ ሊያድን እንዲሁም ሃይማኖት ምግባር ባገኝባቸው ብሎ መጣ ። ነገር ግን ከእስራኤል ዘንድ ሃይማኖት ምግባር አላገኘባቸውም መጋቤ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤልን ምግባር ሃይማኖት ባገኝባቸው ብዬ ስመላለስ እነሆ ሦስት አመቴ (ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በኢየሩሳሌም ዞሮ ያስተማረው ሦስት ዓመት ነው ይህንን ሲያመለክት ነው) ። ነገር ግን ሃይማኖት ምግባር አላገኘሁባቸውም ለሌላው ሕዝብ ምሳሌ ሆነው የእነሱን ምሳሌ ተከትሎ ከእውነተኛው የመዳን መንገድ እንዳይወጣ አጥፋቸው ብሎ ቅዱስ ገብርኤልን ያዘዋል ። መጋቤ ሐዲስ ቅ/ገብርኤልም ለጌታ መልሶ «ጌታ ሆይ ምናልባት ለሚመጣው ዘመን ሃይማኖት በይዙ ምግባር ቢሠሩ እረዳቸዋለሁ ወይም ተራድቼ ሥራ እስኪሠሩቸው ድረስ ለዛሬው ታገሳቸው ። ነገር ግን የእኔን ተራዳኢነትንቀው ወደ ሃይማኖት ወደ ፍጹም ምግባር የማይገቡ ከሆነ ታጠፋቸዋለህ ማለቱ ትዕዛዝህ ተፈጻሚ ይሁን ።

፪ኛ/ «አስቀድሞ ለአይሁዳዊ ደግሞም ለግሪክ ሰው እግዚአብሔር በሰው ፊት አያደላምና» ሮሜ ፪ ፣ ፲፩ እንደተባለው ሁሉ ምሳሌው በአይሁድ ብቻ ተመስሎ የሚያቢቃ አይደለም መላው የአዳም ዘርን የሚያካትት ነው ። ከላይ እንደተጠቀሰው እግዚአብሔር ለአንድ ወገን ብቻ አይደለምና አምላክነቱ ስለዚህ ምሳሌው ለእስራኤል ዘንፍስ ለክርስቲያኖች ሁሉ የተመሰለ ነው ።

ጌታችን በምድር ላይ በሚኖሩ የአዳም ዘሮች ኃጢአት አዝኖ ጠባቂ መላእክቶቻቸውን ጠርቶ «እነሆ ሃይማኖት ምግባር ስፈልግባቸው ይኸው ሦስት ዓመቴ ነው ። ሦስት ዓመት የሚለውን በሰዎች የእድሜ ደረጃ ይመስላል ። የሰው ልጅ አራት የዕድገት ወቅቶች እንዳሉት የታወቀ ነው ። የህጻንነት ፣ ጉርምስና ፣ ጉልምስና ፣ እርግና (እርጅና) እንግዲህ ሦስት ዓመት ሲል ሕጻኑን ትቶ ሌሎች ሦስት የእድገት



www.ethiopianorthodox.org

ደረጃዎችን ሲያመለክት ነው ። ሕጻንነት ንጽሐ ጠባይ የማያድፍበት የፍጹምነት ወቅት ስለሆነ «እውነት እላችኋለሁ፡ የእግዚአብሔርን መንግሥት እንደሕጻን የማይቀበላት ሁሉ ከቶ አይገባበትም አላቸው» ማርቆስ ፲ ፡ ፲፭ በቀሩት በሦስቱ የእድገት ደረጃዎች በየጊዜው ጌታ ወደ እኛ ሕይወት በመንፈስ ይመላለሳል ። በጉርምስናችን ወቅት ህይወታችንን ይጎበኘዋል የቅድስና ሕይወት ያጣል አዝኖ ይሔዳል ከእንደገና ስሜታችን በረድ ባለበት ወቅት ደግሞ ዛሬስ ፍሬ አፍርተው ይሆን ብሎ ህይወታችንን ይጎበኘዋል ። ፍሬ ሃይማኖት የለም ከእንደገና በስተርጅና ዘመናችንም ይጎበኘናል ከርሞ ጥጃዎች አሁንም ሕይወታችን እንደ ጎሰቀለ ነው ። ጌታም ተቆጥቶ ጠባቂ መላእክትን «እነሆ ወደዚህ ሰው ህይወት ስመላለስ ሦስት ጊዜዬ ነው ። ነገር ግን እርሱ ከዛሬ ነገ ፍሬ ሃይማኖት ያፈራል ብዬ ስጠብቀው እየባሰበት ነው ስለዚህ እሱን አብነት አድርገው ሌሎችም ከሃይማኖት ከምግባር በአፉ እንዳይሆኑ አስወግዱት» ብሎ ያዛቸዋል ጠባቂ መላእክትም፣ «አቤቱ ጌታ ሆይ ይህቺን ያሁንዋን ብቻ ታገስ እኛ ተራድተን ምግባር እንዲሠራ እናደርገዋለን ዳሩ ግን ተራዳኢነታችንን ንቆ ምግባር የማይሠራ ከሆነ ታጠፋዋለህ» በማለት በአማላጅነታቸው አማላጅነታቸውን ተራዳኢነታቸውን ጥላ ከለላ አድርጎ ለሚኖር ሰው ያማልዱታል ከመቀስፍም ያድኑታል ። ታዲያ እንዲህ ሲባል አማላጆቻችን ያሰምሩናል እያልን ወደ ፍጹም ምግባር ከመግባት ወደ ኋላ እንድንል አይደለም ። አማላጆቻችንን አማልዱን ስንል ሃይማኖትና ምግባር ይዘን መሆን አለበት አለበለዚያ ራሳችንን በኃጢአት «ውስጥ ሆን ብለን ከተን አማልዱን እያልን ብንጮህ መቅሰፍት ይከተለናል እንጂ ምህረት አይወርድልንም» እግዚአብሔር የሚዘበትበት አምላክ አይደለምና ራስን ከኃጢአት ለማውጣት ሳይጥሩ ቅዱሳንን አማልዱን ማለት በእነርሱም ሆነ በእግዚአብሔርም ላይ ከማሾፍ የተለየ አይደለም ። ስለዚህ የቅዱሳን መላእክትን አማላጅነት ሳናውቅ ለምንሰራው ኃጢአት ሲረዳን አውቀን ስለ ኃጢአታችን አማልደው የሚያስምሩ መላእክት አሉን ብለን ኃጢአት መሥራት ሐኪም ዘመድ አለኝ ብሎ ሆድን በቢላዎ እንደመዘንጠል ይቆጠራል ።

ሉቃ ወን. ፩ ፡ ፲፱ «እኔ በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው መልአኩ ገብርኤል ነኝ»

አየኸውን! የእግዚአብሔር ባለሟል ቅዱስ ገብርኤል ስለባለሟልነቱ ሲናገር «በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ገብርኤል ነኝ»



ሲል በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው ማለቱ በቁሙ ለእግዚአብሔር የተወሰነ ፊት ኖሮት እርሱም እንደ ንጉስ ወታደር በእግዚአብሔር ፊት ተገትሮ የሚቆም መሆኑን አይደለም ። ሊያሳውቅ የፈለገው የእግዚአብሔር ፊቱ ወደ ሁሉም ነው በአራቱም አቅጣጫ ነው ። ቅ/ገብርኤል ሊገልጽ የፈለገው አማላጅነቱን ነው «የእግዚአብሔር ባለሟል የምሆን እኔ ገብርኤል ነኝ» ማለቱ ነው ምንግዜም ከእግዚአብሔር የማይለይ ለዳንኤል ራዕይን የገለጠ እሱ ነውና ። በእግዚአብሔር ፊት መቆም ማማለድን (ባለሟልነትን) የሚገልጽ መሆኑን በመዝሙር ፻፭ (፻፮) ፡ ፳፫ ላይ የምናነበው ነው «የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ» ማለቱ ባያማልዳቸው ኖሮ በባለሟልነቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ባይለምንላቸው ኖሮ ማለት እንደሆነ ከማንም የተሰወረ አይደለም ። እንደዚሁም ቅ/ገብርኤል በእግዚአብሔር ፊት የምቆም ማለቱ አማላጅነቱን ባለሟልነቱን ሲገልጽ ነው ። እንዲሁም መላእክት የትም ቦታ መገኘታቸውን በዚሁ አባባል እንረዳለን የእግዚአብሔር ፊት የትም ቦታ ነው ካልን መላእክትም እግዚአብሔር ባለበት ቦታ ሁሉ ካልጠፋ እሱ ባለበት ቦታ እነርሱም የሚኖሩ ከሆነ የትም ቦታ ብንጠራቸው ይራዱናል ማለት ነው ።

ቅዱስ ጳውሎስ የመላእክትን ተራዳኢነት ሲገልጽ ሰውን ለማገዝ የሚላኩ የሚያገለግሉ ናቸው ብሏል ። ዕብ ፩ ፡ ፲፬ ዛሬ በዚህ ዓለም ሰው የጸለየውን ጸሎት ያቀረበውን መስዋዕት ለማሳረግ ይወጣሉ ይወርዳሉ ኋላ ግን ዋጋቸውን ተቀብለው አርፈው ይኖራሉ ። ዛሬ ግን እኛን በማማለድ ይራዳሉ ።

ቅዱሳን መላእክት በአማላጅነታቸው ለሚተማመኑ ለክርስቶሳውያን ጸሎታቸውን በእግዚአብሔር ፊት ማቅረብ እንደሚችሉና ፍጹም ምሕረት ሊያሰጡ እንደሚችሉ ዮሐንስ በራእይ ተመልክቶታል ። ዮሐንስ ራእይ ፰. ቍ. ፫—፭ ። ሌላ መልአክ ከወደ ምሥራቅ መጣ በታቦቱ (በመሠዊያው) ፊት ቆመ የወርቅ ጽና ይዟል (በቄስ አምሳል ነው ያየው ) በመንበሩ ላይ ባለ በታቦቱ ፊት ለቅዱሳን ጸሎት አምሳል መርገፍ የሚሆን ብዙ ዕጣን ያሳርግ ዘንድ አፍሰው ሰጡት ።

የዕጣኑ ጢስ ለቅዱሳን ጸሎት አምሳል ከመሆን ጋራ ወደ እግዚአብሔር ያረገው በመልአኩ እጅ ነው ። ማዕጠንተ ወርቁን አንሥቶ የኃጥአን ጸሎት አምሳል (ምሳሌ) የሚሆን ኀራረ ዕጣኑን ወደ ምድር



www.ethiopianorthodox.org

ደፋው ወደ ምድር በደፋው ጊዜ ነጐድጓድ መብረቅ ደብልቅልቅ ሆነ አለ ። ኃጢአትን በሠሩ ሰዎች ላይ መቅሠፍት ታዘዘ ሲል ነው ።

አንድ መልአክ የተባለው መጋቤ ብሉይ ቅዱስ ሚካኤል ነው ። የወርቅ ጥና መያዙ ጸሎት የሚያሳርግበትን ሥልጣን ከእግዚአብሔር ማግኘቱን ሲገልጽ ነው ።

. በጎ መዓዛ ያለው ጸሎቱ ከቀደሙት ቅዱሳን ጸሎት ጋራ በሱ ቃል ወደ እግዚአብሔር ዐረገ ። የቀደሙት ቅዱሳን ጸሎትን የሚያሳርግበትን ሥልጣን ከእግዚአብሔር ዘንድ እንደተቀበለ ሁሉ ኃጥአንን የሚያጠፋበትን ሥልጣን ገንዘብ አድርጓል ። ለጻድቃን እንደ ጸለየ በኃጥአን ጸለየባቸው ። በኃጥአን ላይ በጸለየባቸው ጊዜ መቅሠፍት ታዘዘባቸው በአማላጅነቱ ለሚተማመኑ ደግሞ በመጸለይ ምሕረትን አገኙ ።

እንዲሁም ሌላ መልአክ የሚለው መጋቢ ሐዲስ ቅዱስ ገብርኤል ነው ጸሎት በሚያሳርግበት ቦታ ቆመ የምእመናንን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር የሚያሳርግበት ሥልጣን ገንዘብ አድርጓል (ተቀብሏል)

ጌትነቱ በሚታወቅበት ጽኑዕ ፍርድ በሚፈረድበት በዓለም መላእክት በሱ ጸሎት ጸሎተ ቅዱሳን ደኅርትን (የኋለኞቹ ቅዱሳን ጸሎት) በጎ መዓዛ ያለው ዕጣን አድርጎ ያሳርግ ዘንድ አሳርግ አሉት በጸሎቱ በአማላጅነቱ የሚተማመኑ ምእመናን የእርሱ ጸሎት ከጸሎተ ቅዱሳን ደኅርት ጋራ በጎ መዓዛ ያለው ዕጣን ሆኖ በርሱ ቃል ወደ እግዚአብሔር ዐረገ ። የምእመናንን ጸሎት ቅድመ እግዚአብሔር የማሳረግ ሥልጣን እንደተሰጠው ሁሉ ለእግዚአብሔር ወንጌል ለማይታዘዙ ዓመጸኞች ላይም ጸልዮባቸው መቅሠፍት እንደሚያመጣባቸው ሲገልጽ በኃጥአን ጸሎት አምሳል የተመሰለውን ጎራረ ዕጣኑን ወደ ምድር ደፋው ። ያን ጊዜ መነዋወጥ ሆነ ይላል ።

እንግዲህ ክርስቲያኖች ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያናችን መላእክት የእኛን ጸሎት ወደ እግዚአብሔር ያሳርጋሉ የምትለው ከላይ የጠቀስናቸውን የመጽሐፍ ቅዱስ ማስረጃ ይዛ እንጂ ከምንም ትንሥታ አለመሆኑን የተገነዘባችሁ ይመስለኛል ።



## መላእክት ሊሰገድላቸውና ሊከበሩ ይገባቸዋል

ስግደትም ሆነ ክብር በሁለት ወገን ይከፈላል ። ለእግዚአብሔርና ለቅዱሳን ሰዎችና መላእክት ። እግዚአብሔር ብቸኛ ገናና አምላክ ስለሆነ ለእሱ የሚቀርበው ምሥጋና ፥ ክብር ፥ ስግደት ለማንኛውም ፍጡር አይቀርብም በሌላ አንጻር ደግሞ እግዘአብሔር የቀደሳቸውና ያከበራቸውን ደግሞ ከእግዚአብሔር ዘንድ በተሰጣቸው ክብር ልናከብራቸው የፀጋ ስግደት ልንሰግድላቸው መንፈሳዊ ግዴታ አለብን ። «ያዘጋጃቸውን እነሱን ጠራ የጠራቸውን እነሱን አጸደቀ የአጸደቃቸውን እነሱን አከበረ» ሮሜ ፲፫ ፡ ፯ እንግዲህ እግዚአብሔር ያከበረውን ማክበር እንጂ ማዋረድ ለእግዚአብሔር ተገዢ መሆንን አያሳይም «ባለቤቱን ካልናቁ አጥሩን አይነቀንቁ» እንደተባለው እሱ ያከበራቸውን አናከብርም የሚል ካለ ጌታን የናቀ መሆኑን ሊገነዘበው ይገባል ።

የዮሐንስ ራዕይ ፲፱ ፡ ፲ እንዴት ይተረጐማል? አንዳንዶቹ ለመላእክት መስገድ አግባብ አይደለም የሚሉት ይህን ጥቅስ በመጥቀስ ነው ።

በመሠረቱ ይህ ጥቅስ ለመላእክት መስገድ እንዳለብን የሚያስገነዝብ እንጂ አትስገዱ የሚል ሆኖ አናገኘውም የተቃዋሚዎቹ አባባል ስንመረምረው ብዙ ስህተትና ግድፈት እንዳለበት እናምናለን ።

በቅድሚያ ዮሐንስ ለመልአኩ ሳይገባው በስህተት ስግደት አቀረበለት የሚለው አባባላቸው ምን ያህል ከእውነት የራቀና ከመንፈስ ቅዱስ ሥራ ጋር የሚጋጭ መሆኑን እንረዳለን ።

ዮሐንስ ተሳሳተ ይሉ ዘንድ የዮሐንስን ማንነት መጽሐፍ ቅዱስ በሚያስረዳው ሁኔታ የተረዱትና የተገነዘቡት አይመስልም ። የዮሐንስን ማንነት ማወቅ ለፈጸመው ድርጊት ትክክለኛነት ወይም ስህተትነት ሊገልጽልን ይችላል ።

ዮሐንስ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት አንዱ ታዖሎጎስ በሚል ቅጽል የሚጠራ ጥንትና ፍጻሜ የሌለው ዘላለማዊ ገዢ ገባሬ ኩሉ ምሉ ውስተኩሉ የሆነው አምላክ ህልወና ተገልጾለት የጻፈ ጌታ የሚወደው ንጹህ ቅዱስ ድንግል ። በቅድስናው በንጽሕናው በድንግልናው እመቤታችን በአደራ የተሰጣቸው ዮሐ ወን/ ፲፱ ፡ ፳፯ እስከ እግረ መስቀል ድረስ ከጌታ ያልተለየ «እስክመጣ ድረስ ይኑር» ዮሐን ወን/ ፳፩ ፡ ፳፪ የተባለለት በመንፈስ ቅዱስ ተቃኝቶ አካል ከህልውና ተገልጾለት እንኳን ምድራዊው ቀርቶ ሰማያዊው እውቀት ተገልጾ



www.ethiopianorthodox.org

ለት የእግዚአብሔርን አንድነት ሦስትነት የሥጋዌን ምሥጢር አበጥሮ አንጠርጥሮ ያሠፈረ ታላቅ ሐዋርያም ነቢይም ድንግልም ነው ። ይህን ቅዱስ ሰው ስለትንሹ ነገር ለመልአክት መስገድ አግባብ አለመሆኑ ተዘንግቶት ወይም አጥቶት ተሳስቶ ሰግዶ ወቀሳና ማስጠንቀቂያ ተሰጠው ብሎ መናገርና ማስተማር ወደር በማይገኝለት የስህተት ማጥ ውስጥ መግባት ነው ። ምንም እንኳን ሰው እንከን የማይወጣለት ፍጹም በኩለሔ ባይሆንም ነገር ግን ዮሐንስን በዚህ ማግት መንፈስ ቅዱስን መፅረፍ ነው ምክንያቱም በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ሰው «ወደ እውነት ተመርቶ ሌሎችንም ይመራል እንጂ ወደ ስህተት አይመራም ምክንያቱም የተቃኘው ወደ እውነት በሚመራው በእውነት መንፈስ ነውና ዮሐ ወን/ ፲፮ ፡ ፲፪—፲፫ ።

ስለዚህ በጌታችን የእውነት መንፈስ ተብሎ የተመሠከረለት መንፈስ ቅዱስ ዮሐንስን ወደ ስህተት መራው ቢባል በመንፈስ ቅዱስ ላይ የስድብ ቃል መናገር አይሆንም? «መንፈስ ቅዱስን የሰደበ ደግሞ ኃጢአቱ አይሠረይለትም ። ዮሐንስ በመንፈስ ቅዱስ ፀጋ ለመሞላቱ መጽሐፍ ቅዱስ የሚመሰክረው ነው ሐዋ ሥራ ፩ ፡ ፭ ።

በመንፈስ ቅዱስ የተቃኘ ሰው የሚያመልከው ማንን እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል ሌሎችንም ያስተምራል ለማን መስገድ እንዳለበት ጠንቅቆ ያውቃል ። ሌሎችንም ያስተምራል እንጂ ስግደት ለማይገባው ሁሉ ሲንበረከክ አይታይም ። እንኳን ይህን የእግዚአብሔርን ነገር ስንኳ ሳይቀር ያውቃል ፩ኛ ቆሮ ፪ ፡ ፲—፲፪ ።

መንፈስ ቅዱስ የጥበብ ፡ የማስተዋል የምክርና የኃይል የእውቀት መንፈስ መሆኑ በኢሳይያስ ፲፩ ፡ ፲፪ ። ላይ የተገለጸ ነው ። እንግዲህ መንፈስ ቅዱስ በዮሐንስ ላይ አድሮበታል ከተባለ ለመልአክ መስገድ አግባብ አለመሆኑን እንዴት ሳያስተውለው ፡ ሳያውቅ ቀረ ? ከዚህ ሁሉ የምንረዳው ዮሐንስ ለመልአኩ መስገዱ አግባብ ያለው አስፈላጊ መሆኑን ተረድቶ ተገንዝቦ ለእኛ አብነት ሊሆነን እንደሆነ ነው ።

በዚያች ቅጽበት መንፈስ ቅዱስ ተለይቶት ነበር የሚሉ ከሆነ ማስረጃ መጥቀስ አለባቸው ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ከሐዋርያት የተለየበት ወቅት በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጠቀሰም በጸርሐ ጽዮን በእሳት አምሳል ፀጋው ከታደላቸው በኋላ ጌታ በተናገረው መሠረት «እርፍ ይዞ ወደኋላ የሚያርስ ገበሬ የለም» የሚለውን አባባል ይዘው እስከ ሞት የታመኑ መሆናቸው ነው የተዘገበው ጌታም «እስከ ዓለም



ፍጻሜ ከናንተ ጋር ነኝ» ማቴ ፳፰ ፡ ፳ ብሎ ተናገረ እንጂ አለያችኋለሁ አላለም ።

ምነው ሳ ዮሐንስ መጥምቅ በወህኒ ሆኖ ስለ ክርስቶስ መጠየቁ መንፈስ ቅዱስ እንደተለየው የሚያረጋግጥ አይደለም ቢሉ አይደለም ዮሐንስ መጥምቅ ደቀመዛሙርቱን ወደ ጌታ ዘንድ መላኩ እሱ ስለጌታ ማንነት ተጠራጥሮ ሳይሆን የላካቸው ሰዎች ተጠራጥረው ነበርና አይተው አምላክነቱን ይረዱት ብሎ ነው እንጂ ። እርሱስ ያጠመቀውን የመሰከረለትን ሊያጣው እንዴት ይችላል? ማቴ ፲፩ ፡ ፪ ።

እንግዲህ ከላይ በተዘረዘረው ሁኔታ ዮሐንስ ለመልአኩ የሰገደው አግባብ መሆኑን ተረድቶ ነው ። ከተባለ መልአኩስ አትስገድልኝ ማለቱ ስለምንድን ነው?

መልስ ፡— ስለ ሦስት ነገር አትስገድልኝ ብሎታል ።

1ኛ/ <u>ስለ ትህትና</u> ፡—

ሚካኤል ቢሉ ስሙ እንደሚጠቁመው ሚ ፡ መኑ ፡ ካ ፡ ከመ፤ኤል አምላክ በተገናኘ መኑ ከመአምላክ ማለት ነው በአማርኛ እንደ አምላክ ያለ ማነው ማለት ነው (41) ስለዚህ ሚካኤል መባሉ በትህትናው አምላኩን በመምሰሉ ስለሆነ ለትህትና ብሎ አትስገድልኝ ብሎታል ። ሰዎች እርስ በርሳቸው ትህትና ሲለዋወጡ አይገባም አይገባም እንዲባባሉ ሁሉ መልአኩም አይገባኝም ማለቱ ነው ለትህትና ባይሆን ኖሮ በምዕራፍ አሥራ ዘጠኝ አስጠንቅቆት ሳለ ምዕራፍ ሃያ ሁለት ላይ በድጋሚ ሲሰግድ ሕገ እግዚአብሔርን በመጣሱ በሰይፍ በቀላው ነበር ። ነገር ግን አግባብ አይደለም ማለቱ ስላልሆነ በድጋሚ ሲሰግድለትም አሁንም የትህትናን ነገር ነው የተናገረው ቅዱሳን ምንግዜም ቢሆን እንደሰይጣን አክብሩን አይሉምና ክብር ሁሉ ለእግዚአብሔር ብቻ እንደሚገባ ያምናሉ እግዚአብሔር ግን እንዲከበሩ ያደርጋቸዋል ።

2ኛ/ <u>ስለ ዮሐንስ ክብር ሲል ነው</u> ፡—

ዮሐንስ በክብር ከመልአኩ እኩል ሆኖ ስለነበር ይህንን ክብሩን ሊገልጽለት ስለፈለገ መልአኩ አንተኮ ከእኔ ጋር በክብር እኩል

(41) አለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ መዝገበ ቃላት ገጽ 589



www.ethiopianorthodox.org

ነህ ታዲያ እንዴት ትሰግድልኛለህ እባክህ ተገቢዬ አይደለም ሁላታች ንም ለእግዚአብሔር እንስገድ ሲል ነው ስግደት የበላይና የበታችነትን የሚያመለክት ስለሆነ ።

3ኛ/ ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል ነው

ብርሃነ ዓለም ጳውሎስ «ካህናት ሰውን ሁሉ እንደሚዳኙ አታው ቁምን እናንተ ሰውን ሁሉ የምትዳኙ ከሆናችሁ ይህን የትንሹን ነገር ልትፈርዱ አይገባችሁምን ። የዚህንስ ዓለም ዳኝነት ተውትና መላእክ ትን ስንኳ እንድንገዛ አታውቁምን» ፩ኛ ቆሮ ፮ ፥ ፪—፫ ።
በማለት የካህናት ሥልጣን ምን ያህል የከበረና የገነነ መሆኑን ገልጾ አል ይህን በማስመልከት አንድ ታሪክ ይተረካል ስለ ዮሐንስ አፈወርቅ ነው ።

በ344 ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተማ አትናስያና ሲፋንዶስ ከተባሉት ባልና ሚስት የተወለደው ዮሐንስ አፈወርቅ የመጀመሪያ ሥራው ጥብቅና ነበረ የኋላ ኋላ ግን ይህ ሥራ ስላላረካው ማናቸውንም ነገር ትቶ ክርስቲያን መሆንን ወደደና ከአንጾኪያ ኤጲስ ቆጶስ ከመሊትስ ዘንድ ሦስት ዓመት ከተማረ በኋላ ተጠመቀ ። በተወለደ በ30 ዓመቱ በእናቱ ሞት ምክንያት የአንጾኪያን ከተማ ለቆ ወደ ሌላ አገር መንኖ መነኮሰ ከመነኮሰ በኋላ ሁለት ዓመት በዋሻ ተቀመጠ ብዙ መንፈሳዊ መጻሕፍትን ጻፈ በ380 ዓ. ም. በህመም ምክንያት ወደ አንጾኪያ ተመልሶ ከኤ ጲስ ቆጶሱ ከመሊቲየስ ድቁና ተቀበለ ። ዮሐንስ በብህት ውና ሊያሳልፍ ቢሆንም የመጀመሪያ ሐሳቡ የኋላ ኋላ ግን ወንጌልን ለሕዝቡ መስበክ እንዳለበት ሙረጠ ። እምነትንና ፍቅርን ትእግሥት ንና ትሕትናን በአንድነት ገመዱ አስሮ ለሕዝቡ 7 ዓመት ወንጌልን ከሰበከላቸው በኋላ በ387 ዓ.ም. በአንጾኪያ ከተማ ፓትሪያርክነት ተሾመ (42)

ዮሐንስ በአንጾኪያ ከተማ 12 ዓመት ሲሰብክና ሲያስተምር ኖረ ። በዚያን ዘመን እንደ ዮሐንስ ስብከትን አሳማሪ እውነትን ተና ጋሪ ተነስቶ አያውቅም ይባላል ። በቤተ ክርስቲያን በበዓል ቀን ሕዝቡ

(42) ፓትሪያርክ ማለት የግሪክ ቋንቋ ሲሆን ፓተር ወይም ፓትር አባት ማለት ነው ። ያርክ ማለት መዠመሪያ ወይም በር ከፋች ማለት ነው ፓትሪያርክ የመዠመሪያ አባት ወይ የመዠመሪያ በር ከፋች ማለት ነው ።
(43) መጽሔት አሚን ገጽ 57 — 59



ሲሰበሰብ በቀኝና በግራ እየተንጐራደደ ሲሰብክ ሕዝቡ በሰሙ ጊዜ ከደስታቸው ብዛት የተነሣ ገሚሱ ሲስቅ ገሚሱ ያለቅስ ነበር ። ይባ ላል የዮሐንስንም ስብከት ለመስማት የሚሰበሰበው ሕዝብ እስከ 2 እልፍ ይደርስ ነበር እሑድ እሑድ ቀርቶ በዘወትር የሚሰበሰበው ሕዝብ ልክ የለውም ነበር ። ከስብከቱና ከአነጋገሩም ጣዕም የተነሣ ሕዝቡ ዮሐንስ አፈወርቅ ብለው ሰየሙት ይባላል ። በተአምረ ማርያም ላይ አፈወርቅ የተባለበት ሌላው ምክንያት ሰፍሮአል ።

ሐሊናው በመንፈሳዊ ሐሳብ ተገርቶ የክርስቶስ ሁኔታ ምሥጢሩ ልብ በሚነካ ስብከት እየገለጸ ከወርቅና ከብር ይልቅ የከረረ እምነትንና እውነትን ስለተናገረና ስለአስተማረ ሕዝቡ ሁሉ አፈወርቅ ወይም አፈ ዕንቁ ብለው ሰይሙት ይባላል (43)

ከላይ ያለው ታሪክ ለዋናው ነጥባችን መነሻ ይሆን ዘንድ ነው ። አሁን ወደተፈለገው ሐሳብ እንዝለቅ ለዚሁ ለዮሐንስ አፈወርቅ ሁለት ወዳጆች ነበሩት ። ንጉሡ አርቃድዮስ ንግሥቲቱ አውዶክስያም ይባ ላሉ ልጅ እየወለዱ ይሞትባቸዋል በምን ምክንያት ልጅ እንደማያድግ ላቸው ሲጠይቁ ደግ ሰው ክርስትና ቢያነሣላችሁ ይሆናል አሏቸው ። ከዮሐንስ አፈወርቅ የበለጠ ደግ ሰው አለን ብለው ሴት ልጅ በወለዱ ጊዜ መጥተህ ክርስትና አንሳልን ብለው ላኩበት ። እርሱም ጥሪውን አክብሮ ሲሔድ በመንገድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ከተላከ መልአክ ጋር ይገናኛል ። የበቃ ነውና ሊያየው ችሎአል ። ዮሐንስም መልአኩን ወዴት ትሔዳለህ ብሎ ጠየቀው መልአኩም ሲመልስለት አሁን አንተ የምትሔድበትን ብላቴና ነፍሷን ከሥጋዋ ለይተህ አምጣ ብሎኝ የታ ዘዝኩትን ለመፈጸም ወደዚያ መሔዴ ነው ይለዋል ገናናትና ቆየኝ ላጥምቃት ሀብተ ወልድና ስመ ክርስትና ከተሰጣት በኋላ የታዘዝከ ውን ትፈጽማለህ እስከዚያው ግን ከዚሁ አትንቀሳቀስ ብሎት በስል ጣነ ክህነቱ ገዝቶት ሄደ መልአኩም የዮሐንስን ግዝት ጠብቆ ባለበት ቆመ ። ዮሐንስ ልጅቷን አጥምቋት ረስቶት በሌላ መንገድ ተመለሰ ።

የካህናት ሙዓረጋቸው ደግ እንደሆነ ስለሚያውቅ ያ መልአክ ወደ ላይም ወደታችም ሳይል አሥር ዓመት ከዚያው ሥፍራ ቆሞ ኖረ ። አሥር ዓመት ሲሆናት ለባል ታጨች ያጠመቅካት ብላቴና እነሆ ለአቅመ ሄዋን አድርሳ ባል ልታገባ ነውና መጥተህ ባርከህ ስደ ዳት ብለው ለዮሐንስ አፈወርቅ ላኩበት ። እርሱም በጥሪው መሠረት የዛሬ አሥር ዓመት ልጅቱን ሊያጠምቅ ሲሔድ በሔደበት መንገድ



www.ethiopianorthodox.org

ቢሔድ መልአ[ከ]ን ቆሞ አገኘው ። «ምነው ከዚህ ቆመሃል አለው?» መልአኩም ሲ[መ]ልስለት «የካህናት መዓረጋችሁ የከበረ ነውና ሙች ወዲያ ወዲህ ያሰኛል ቃልህን አክብሬ አንተ ቆይ ካልከኝ ወዲህ ወዲያና ወዲህ ብዬ አላወቅም» አለው ከዚያም ዮሐንስ በዝንጉነቱ ራሱን ወቅሶ መልአኩን የታዘዘበትን ያደርግ ዘንድ አሰናብቶታል ። (44)

ከዚህ ታሪክ የምንረዳው ቢኖር የሥልጣነ ክህነትን ክቡርነት ነው ። እንግዲህ መልአኩም ለዮሐንስ ወንጌላዊ አትስገድልኝ ማለቱ ዮሐንስ ካህን ስለነበረ ስለ ሥልጣነ ክህነት ክብር ሲል በሥልጣነ ክህነት እንደሚበልጠው ሊያስገነዝበው ሽቶ ነው እንጂ ኃጢአት ሆኖ ለጣኦት እንደመስገድ የሚቆጠር ሆኖ አይደለም እንዲህማ ቢሆን ኖሮ ከታች [በ]ተጠቀሱት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ብዙ ቅዱሳን ሰዎች ለመላእክት ባልሰገዱ ነበር ።

— ኦሪት ዘፍ. ፲፱ ፡ ፩—፱ «ሎጥ በግምባሩ ተደፍቶ ለመላእክት ለሚካኤልና ለገብርኤል እንደሰገደ ተዘግቧል ሁለቱ መላእክት ስህተት ሰርተሃል ለእኛ መስገድ ከፈጣሪ ጋር ያጣላሀል አላሉትም ።

መጽ. ኢያሱ ፭ ፡ ፲፫ «ኢያሱ ለመላእክት አለቃ ለቅዱስ ሚካኤል ሲሰግድለት ቅዱስ ሚካኤል አትስገድልኝ ተጠንቀቅ አላለውም ። ኢያሱም ለመላእክት አለቃ ለቅዱስ ሚካኤል መስገዱም አግባብ መሆኑን አውቆ ነው እንጂ ተሳስቶ ወይም ደንግጦ አይደለም «እኔና ቤቴ እግዚአብሔርን እናመልካለን ። የምታመልኩትን ከአሁኑ ምረጡ» በማለት አምልኮቱ በአንድ እግዚአብሔር ላይ ብቻ መሆኑን አረጋግጦአል ።

— ዜና መዋዕል ቀዳ. ፳፩ ፡ ፲፮ ዳዊትና ሽማግሌዎች ለመልአኩ በግምባራቸው ተደፍተው መስገዳቸው ተገልጾአል ። እንግዲህ ዳዊት ተገቢ ያልሆነ እግዚአብሔርን የሚያሳዝን ሥራ ሠራ ሊሉት ይደፍራሉ ።

— ትንቢተ ዳንኤል ፰ ፡ ፲፯ «ዳንኤል ለቅ/ገብርኤል ሁለት ጊዜ ሰግዶለታል ። ደንግጦ እንጂ ወዶ ፈቅዶ ያደረገው አይደለም የሚሉ

(44) የቅ ጳውሎስ መጽ ንባቡ ከነትርጓሜው ገጽ 210



ከሆነ ታዲያ ለምን በናቡከደናጾር ቁጣና በአንበሶቹ ጉድጓድ ትጣላለህ በተባለ ጊዜ ደንግጦ ለጣኦት አልሰግድም እግዚአብሔርን አልካደም? ዳንኤል በድንጋጤ ከአምልኮተ እግዚአብሔር የሚያወጣ ሥራ አልሠራም ቢሠራ ኖሮ በእግዚአብሔር ዘንድ ክብር ሳይሆን ውርደት በጠበቀው ነበር ። ደግሞም መላእክት ግሩምና አስደንጋጭ ግርማ እንዳለባቸው ካመኑ ለምን አያከብሩአቸውም በፍጥረታቸው ሳንወድ በግድ ከመደፋታችን በፊት ወደን ፈቅደን ክብራቸውን አውቀን የፀጋ ስግደት አንሰግድላቸውም? አይ ሲገለጹ ብቻ ነው ሊሰገድላቸው የሚገባው አሁን ግን በሌሉበት እንዴት ይሰገዳል የሚሉ ከሆነ ደግሞ እግዚአብሔርን ያምናምነው በዓይናችን ስላየነው አይደለም ነገር ግን የነቢያትን የሐዋርያትን ዓይን የእኛ ዓይን አድርገን የእነሱን እጅ የእኛ እጅ አድርገን በፍጹም ሃይማኖት እንዳየነው እንደዳሰስነው አድርገን እናምናለን እንጂ ካላየነው በስተቀር አንሰግድለትም አናምነውም ብንል የእምነት ሰዎች አንባልም፡ «ሳያዩ የሚያምኑ ብጹአን ናቸው» ዮሐን. ወን. ፳ ፡ ፳፱ ተባለ እንጂ አይተው ዳሰው ያመኑ ብጹአን ናቸው አልተባለምና እኛም በብሉይ ኪዳን የነበሩ አበውን ዓይን ዓይን አድርገን የብሉይ ኪዳንን ህግና ትምህርት እንደተቀበልን እንዲሁም የሐዋርያትን ዓይን ዓይናችን አድርገን ሐዲስ ኪዳንን እምነን እንደተቀበልን ሁሉ የቀደሙት ቅዱሳን አበው በተገለጹላቸው ጊዜ ለቅዱሳን መላእክት እንደ ሰገዱላቸው የጸጋ ስግደት መስገድም ተገቢ መሆኑን ስላስረዱን መላእክትን በዓይነ ሥጋችን ባናያቸውም መኖራቸው ግን የማይታበል ሐቅ ስለሆነ የፀጋ ስግደት በስዕላቸው ፊትም ሆነ በስማቸው በታነፀ ቤተክርስቲያን ሄደን በመንፈስ (በእምነት) እንሰግድላቸዋለን «እግዚአብሔር መንፈስ ነው የሚሰግዱለትም በመንፈስ ሊሰግዱለት ይገባል» ዮሐን. ወን. ፬ ፡ ፳፬ እንየደተባለው ሁሉ «የእግዚአብሔር መናፍስት» ራዕይ ፬ ፡ ፭ ተብለው ለተጠሩት መላእክትም በመንፈስ (በእምነት) የፀጋ ስግደት እንሰግድላቸዋለን። ተገልጾላቸው በነበረ ጊዜ የሰገዱላቸው ቅዱሳን አበው ያገኙትን ጸጋ እኛም እናገኘዋለን ። እምነት ይበልጥ ፀጋን የሚያሰጠው ሳያዩ ሲያምኑና ሲታመኑ ነው ።

## ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ መልአክ (ሚካኤል) ነው ?

በመሠረቱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ክብር ምሥጋና ይግባውና የመላእክት ፈጣሪ እንጂ ከመላእክት ጋር የሚደመር ፍጡር አይደለም ። ሰይጣን ያደረባቸው ሰዎች ግን የባሕርይ አምላክ የሆነውን



www.ethiopianorthodox.org

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ከሚካኤል ጋር አንድ አድርገው ሲናገሩ ይሰማሉ ። እንዲህ ዓይነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሆነ ትምህርት የሚያስተምሩት አርዮሳውያን ናቸው ።

አርዮሳውያን ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸው ትምህርት ከዚህ እንደሚከተለው ባጭሩ ተገልጾአል ።

<u>ክርስቶስ ሰው ከመሆኑ በፊት (Prehuman State)</u>
በዋችታወር ሶሳይቲ እምነት ክርስቶስ (ሚካኤል) የመጀመሪያው የይሖዋ ፍጡር ነው ። ይህንንም እምነታቸውን እንዲህ ሲሉ ይገልጡታል «ኢየሱስ ወደ ምድር ከመምጣቱ በፊት መላእክት ያላቸው አይነት መንፈሳዊ አካል ነበረው» (45)

በእነሱ እምነት እንግዲህ ከሥጋዌ በፊት ፍጹም መልአክ ነበረ ማለት ነው ። ሚካኤል በሚል ስም ይታወቅ ነበር ይላሉ ። በይሁዳ መል ፩ ፤ ፱ ላይ ስለ ሙሴ ሥጋ የተከራከረው መልአክ ሚካኤል ክርስቶስ ነው ለይሖዋ ታዛዥ ሆነ ። ይላሉ ።

<u>ሰው በሆነ ጊዜ (The Hman State ፡)</u> የክርስቶስን ሰው መሆን ሲናገሩ «ይሖዋ የልጁን ሕይወት ከሰማይ ወስዶ በማርያም ማህፀን ወስጥ አስቀመጠው ። ሌሎች ልጆች በእናታቸው ማህፀን እንደሚያድጉ ሁሉ ኢየሱስም በማርያም ማህፀን ውስጥ ማደግ ጀመረ (46) በማለት ሚካኤል በሚል ስም ይጠራ የነበረው መልአክን ይሖዋ ሰው እንዲሆን እንደወሰነና ከመልአክነቱ አዋርዶ ሰው እንዳደረገው ያስተምራሉ ።

ስለዚህ ክርስቶስ ምንም እንኳን የይሖዋ ቃል ተብሎ ቢጠራም ከይሖዋ ጋር በፍጹም የተካከለ አይደለም ። ነገር ግን ለአምላክ ታዛዥ በመሆኑ የተንጣ የፀጋ አምላክ አድርጎታል ይላሉ ። ሰው ሆኖ በምድር ላይ በኖረበት ጊዜ መንፈሳዊ ሰው (Spirit Person) አል ነበረም ሰው ብቻ ነበረ ሲወለድም ፍጹም ሰዋዊ ፍጡር ሆኖ ነው ልክ እንደ መጀመሪያው ፍጡር እንደ አዳም ይላሉ ።

---

(45) ታላቁን አስተማሪ ማዳመጥ ገጽ 172
(46) ታላቁን አስተማሪ ማዳመጥ ገጽ 24



<u>ከሥጋዌ በኋላ (The Posthuman)</u> ፤ ይሖዋ ክርስቶስን ከሞት ባሳነሰው ጊዜ ታላቅ ኃይል መንፈሳዊ አድርጎ ነበር ያስነሳው በተነሳበትም ወቅት በሥጋው ሳይሆን በማይታይ መንፈሳዊ አካል ነው ይላሉ ሥጋውንስ በየት አኖረው ለሚለው ጥያቄ መልስ ሲሰጡ ደግሞ እንደ ሙሴ ሥጋ ይሖዋ በፈለገው መንገድና ሁኔታ በአንድ ቦታ አስቀምጦታል ። ሩዘርፎርድ የተባለው የዋችታዎር ሶሳይቲ ሁለተኛው ፕሬዘዳንት ደግሞ ስለ ክርስቶስ ሥጋ ሲናገር «ለወደፊቱ በምትመሠረተው (በ1000 ዓመት) ማለት ነው የምድር አገዛዝ ለተመረጡ ሰዎች በኤግዚቢሽንነት ይታያል ብሏል (47)

አርዮሳውያን ስለ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያላቸውን እምነት ባጭሩ ስንገልጸው

መልአክ — ሰው — መልአክ በሦስቱ መካከል ምንም ዓይነት ግንኙነት የለም መጀመሪያ መልአክ ነበረ ቀጥሎ በይሖዋ ትዕዛዝ ፍጹም ተዋርዶ ሰው ሆነ መልአክነቱን አጥቶ ቀጥሎም ታዛዥ በመሆኑ ከበፊቱ መንፈሳዊ ፍጡርነቱ የበለጠ ክብር አግኝቶ ልዩ መልአክ ለወደፊቱ ለምትመሠረተው አዲሲቱ ዓለም ንጉስ ይሆን ዘንድ የታጨ መልአክ ሆነ ።

ከላይ የተጠቀሰው የአርዮሳውያን ትምህርት ፍጹም ከመጽሐፍ ቅዱስ የራቀ ኢክርስቲያናዊ ትምህርት ነው ።

ጳውሎስ ወገኖቹ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስን ምን ብለን እንመነው መልአክ ነው ብለን እንመነው ባሉት ጊዜ ስለ ጌታችን ማንነት ሲያስረዳ «ከሆነ ጀምሮ ከመላእክቱ ማንን አለው አንተ ልጄ ነህ እኔም ዛሬ ወለድኩህ ዳግመኛም አለ እኔ አባት እሆነዋለሁ እሱም ልጄ ይሆነኛል ። ዕብ ፩ ፡ ፭ ብሎ ጌታችን ከመላእክት የተለየ መሆኑን ካስረዳ በኋላ ስለ ጌታችን ሲናገር ደግሞ «ዳግመኛ በኩርን ወደ ዓለም በሰደደው ጊዜ የእግዚአብሔር መላእክት ሁሉ ይሰግዱለታል» ብሎ መላእክት ሁሉ የሚሰግዱለት የሚንበረከኩለት እንደሆነ ገልጾአል ።

---

(47) The Harp. of God P. 173



www.ethiopianorthodox.org

የመላእክት ፈጣሪ መሆኑን ሲገልጽም «ስለ መላ እክቱም አለ መላእክ ቱን ነፋሳት የሚላኩትንም የእሳት ነበልባል የሚያደርጋቸው» ይልና ስለ ጌታ መልአክ አለመሆን ሲያስረዳ ደግሞ «ስለ ልጁ ግን አለ ጌታ ሆይ ዙፋንህ ለዘላለም ነው የመንግሥትህ በትር የጽድቅ በትር ነው» ብሎአል ። ስለ ፈጣሪነቱም ሲገልጽ «ዳግመኛም እንዲህ አለ አቤቱ አንተ አስቀድሞ ምድርን ፈጠርክ ሰማያትም የእጆችህ ሥራ ናቸው» በማለት «እግዚአብሔር ሰማይና ምድርን ፈጠረ» ከሚለው ጋር አቆራኝቶ ነገራቸው «እነሱ ያልፋሉ አንተ ግን ትኖራለህ ሁሉ እንደ ልብስ ያረጃል (ፍጡር ናቸውና) እንደ መጋረጃም ትጠቀልላቸዋለህ ይለወጣሉም አንተ ግን መቼም መቼ አንተ ነህ (ከእግዚአብሔርነቱ ተለውጦ እንደማያውቅ ሲናገር ነው) ዘመንህም የማይፈጸም ነው ። ከሆነ ጀምሮ ከመላእክት ማንን አለው? በቀኝ ተቀመጥ? ማንንም አላለም ብሎ መልአክ ነው ለሚሉት የማያወላዳ መልስ ሰጥቶአል ዕብ ፩ ፥ ፳—፲፬ ።

ደግሞም ጳውሎስ የክርስቶስንና የሚካኤልን አንድ አለመሆን ሲያስረዳን «ጌታችን ከሰማይ ይወርዳል በሊቀ መላእክት ቃል በእግዚአብሔር መለከት ድምጽም ያዝዛል» ፩ኛ ተሰሎንቄ ፬ ፥ ፲፮ ። ብሎ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሚካኤል ጌታ ፈጣሪ እንደሆነና ሚካኤልም የእሱ ታዛዥ መሆኑን ገልጾአል ።

በዮሐንስ ራዕይ ፲፪ ፥ ፩—፲፯ ። ባለው ላይ የጌታችንና የሚካኤልን ልዩነት ግልጽ ሆኖ ሰፍሩአል ።

ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እግዚአብሔር ነው ። ስለ ሁላችን ኃጢአት ሲል የሰውን ሥጋ ተዋህዶ በቀራንዮ አደባባይ የተሰቀለ የሞተ ሞትን ድል አድርጎ የተነሣ የባህርይ አምላክ ነው (48)

(48) ኢሳ 45 ፥ 20—24 ትን ሆሴ 13 ፥ 4 ቲቶ 2 ፥ 12—13 ሐዋ 4 ፥ 12 ሉቃ 2 ፥ 11 ትን ኢሳ 9 ፥ 6 ራእይ 1 ፥ 8, ራእይ 22 ፥ 12 ኢሳ 40 ፥ 10 የሐዋ ሥራ 1 ፥ 9 መዝ 46 (47) ፥ 5 መዝ 49 (50) ፥ 2 ዮሐ ወን 1 ፥ 1 ሮሜ ፥ 5 1ኛ ዮሐ 1 5 ፥ 20—21



## ማ ጠ ቃ ለ ያ

- ቅዱሳን መላእክት የተፈጠሩት በዕለተ እሁድ ነው መዝ ፻፴፰ ፥ ፪—፳ ።
- መላእክት ለምሕረትና ለመዓት ይላካሉ ። በአማላጅነታቸው ለሚተማመኑት ሰዎችም ከእግዚአብሔር ዘንድ ያማልዳሉ ።
- መላእክት አያገቡም አይጋቡም ማቴ ፳፪ ፥ ፴ ።
- መላእክት ረቂቃን አካላት ናቸው ።
- ሊቃነ መላእክት ሰባት ናቸው ራዕይ ፬ ፥ ፮



www.ethiopianorthodox.org